"ወጡ ሳይወጠወጥ ወስከንባዩ ቁጢጥ!"

**ፀሃዬ ደባልቀው - ዋሺንግተን ዲሲ**

December 6, 2013

ሰሞኑን አንድ አስቂኝ ድራማ ከወደዚህ ከዋሺንግተን ዲሲ መሰማቱን እንደ ተረት ተረት የልበ ወለድ ስላቅ ቢጤ ስላለፈው አንድ ጉዳይ ላጫውታችሁ ወደድኩኝ ፡፡

ጉድ ሳይሰማ ሌሊቱ አይነጋማ ብላችሁ ከመወትወታችሁ በፊት ጨዋታው ወዲህ ነው "ሰሞኑን ኢሳት በተሰኘው on-line-TV (የድረ-ገጽ መስመር ቴሌቪዥን ) ከታወቀው የምድር ቤት (Basement) ስቱዲየው የሽብርተኛውን የግንቦት 7 ሊቀመንበር የሆኑትን የዶ/ር ብርሃኑ ነጋን ያዙኝ ልቀቁኝ አይነት ቅጥ ያጣ ለያዥና ለገራዥ የማይመቸውን ጉራቸውን ሲቸረችሩና ማለቂያ የሌለው ዲስኩራቸውን ሲቀዱ ማስደመጡን ልብ ይሏል፡፡

እንደ እሳቸው እምነት ግንቦት 7 ግዙፍና የታጠቀ፣ አልፎ ተርፎም አስጨናቂ ድርጅት በመሆኑና ኢህአዴግን በታጠቀው "ሕዝባዊ ሀይል" አማካኝነት የመርፌ ቀዳዳ ታክል እንኳን መተንፈሻ ስላሳጣው "እባክህን ግንቦት 7 ሆይ ማረኝ ብሎ" የእንደራደር ልመና መልእክትና ጥያቄ ያቀረበለት ስለመሆኑ ነበር ከዙፋናቸው ላይ ጉብ ብለው ትንተና አዘል ዲስኩራቸውን የለቀቁብን የዓመቱ አስቂኝ ትወና ሆኖ እንደሚያልፍም ነገር አዋቂዎች የደመደሙት ጉዳይ ነው "የጅብ ችኩል ቀንድ ይነክሳል" አይደል እሚባለው?

ለማስታወስ ያህል አንድ የታሪክ ሰበዝ ልምዘዝና እኒህ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋኮ የመጀመሪያ ጊዜያቸው አይደለም እንዲህ ነገረ አለሙ ተምታቶባቸው ሲዘባርቁ የዛሬ ስንትና ስንት ዓመት በፊትኮ የዋሁን ዳያስፖራ በሉ ወገኖቼ መስከረም ሲጠባ መስቀል አደባባይ ላይ እንገናኛለን ባዲስ አበባ በማለት እዛው አደባባይ ላይ "የጀግና ተመላሽ የምስክር ወረቀት" እንደሚሰጥ በማወጅ እያንዳንዱን በ$500 ዶላር ቸብችበው ዶላሩ የት ይግባ የት ሳይጠየቅ ቁሱም ዝም መጽሃፉም ዝም ሆኗል፡፡ ዶ/ሩ ከዚያ በኋላ ብዙ ቅጥፈቶችን እየማሉ እየተገዘቱ ሲዘከዝኩ ይኸውና ሰሞኑን ተወዳዳሪ የማይገኝለት ለከት የለሽ ጉራቸውን በውሸት ጆብነው አቀረቡልን፡፡

ቁና ቁና እየተነፈሱ ያኔ የኤርትራው መንግሥት ለተላላኪነታቸው ውለታ የሚሆን $500 ሺህ ዶላር ድጐማ አርጎልናል ብለው ያላንዳች ሀፍረት ዓይናቸውን በጨው አጥበው አልነበርና በአደባበይ ጉራ ከረዩ ሲሉ የተደመጡት?

ለዚህ ሁሉ አለሁ አለሁ ባይነት መንስኤው የግንቦት 7 መሪዎች ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ እንዲሉ፤ ጀግንነት አርበኛነትና ታጋይነት በውሸት ነቢብ ይደነድኑ ይመስል አንዳችም በገቢር የሚታጀብ ሥራ ሳይሰሩ የባጥ የቆጡን መቀባጠራቸው ይመስለኛል፡፡

አንዴ ኢህኢዲግ የግንቦት 7 አመራሮችን ሊገድል ሲል አከሸፍንበት፣ በማለት ሲዘባርቁ ተደምጠው ነበር፡፡ ድሮም ቢሆን እንደከብት ጭራ እየተከተሉ መቃወምንና ማጣጣልን እንጂ የራሳቸው ኘሮግራም፣ ስትራቴጂና ፖሊሲ በአማራጭነት ለሕዝቡ አቅርበው ሕዝብ ብይኑን እንዲሰጥ የማድረግ

ብቃቱም፣ ዝግጁነቱም ስለሌላቸው አሁን ደግሞ ተንደርድረው አቅጣጫዋን እንደሳተች መርከብ በአጀንዳ እጦት ወዲያ ወዲህ ሲላተሙ ይስተዋላሉ።

"አሁንም የሰማሁት ነገር በነዚህ በተቃዋሚዎች የውሸት ወናፍ ቢሆንም " ዶ/ር ብርሃኑ ኢህአዴግ አቀረበልን ስላሉት የድርድር ጉዳይ ተጠይቀው ሲመልሱ አቶ ሽመልስ ከማል የመንግሥት ኮሙዩኒኬሽን ም/ሚኒስትር እንዲህ አሉ የሚለው ነው። " መንግሥት ለግንቦት 7 ምንም ዓይነት የእንደራደር ጥያቄ አላቀረበም። " ኢህአዲግ የድርድር ጥያቄ አቅርቦልናል በሚል ግንቦት 7 እያናፈሰ ያለው መሠረተ ቢስ የፈጠራ ወሬ ነው። መንግሥት መደራደር ቢፈልግ ጌታው እያለ ከተላላኪ ጋር ምን ያደራድረዋል ሲሉ የግንቦት 7ን የኤርትራ መንግሥት ሎሌነት አጋልጠዋል። ግንቦት 7 ለምን ይኸንን የፈጠራ መንገድ መረጠ የሚለውን ጥያቄ ማንሳቱ ተገቢ ይመስለኛል። ድሮም የህዝብ ድጋፍ የሌለው በሕዝቡ መሃል ሆኖ ዳገት መውጣትና ቁልቁለት መውረድ የማይጠጋው ባጭሩ በበሬ ወለደ ኘሮፓጋንዳ እንደ ጌታው እንደ ሻእቢያ ሁሉንም ማካካስ የሚቻል የሚመስለው በተግባር የሌለ ነገር ግን አለሁ አለሁ ባይ ወጡ ሳይወጠወጥ ወስከንባዩ ቁጢጥ ዓይነት ግብዝ ነው።

"እውነትም ሳይጠሩት አቤት ሳይልኩት ወዴት" በማለት ጽሑፌን ቋጠርኩ። ከጥቂት ጊዜያት በኂላ በራሴ ምህዋር ውስጥ ሆኜ ሰሞኑን በአንድ የተቃዋሚ ድረ-ገጽ ያነበብኩት ትዝ አለኝ። ይኸውላችሁ ላካፍላችሁ Ethiopian Review የሚባለው ድረ ገጽ ምን ይዞ ብቅ አለመሰላችሁ?

The wall street Journal, Transparency international Releases first comparable corruption Index በሚል ርእስ ጉዳይ ላይ Risk and compliance journal በሚል አምዱ ሥር Samuel Rubenfeld የጻፈውን መጣጥፍ ምንጩንና ፀሐፊውን ሳይጠቅስ ሲያወጣ " በሙስናና በንቅዘት የተጨማለቁ 10 አገሮችን ይዘረዝርና በሌላ በኩልም ሙስናና ንቅዘት በተጻጻሪነት ያልበላቸው ብሎ ሌሎች 10 አገሮችን ይዘረዝራል ልብ በሉ ሁለቱም መዘርዝር ውስጥ ኢትዮጵያ" የምትባል አገር አልተካተተችም እጅግ በሙስና የተጨማለቁትም ይሁን ከሙስና ነጻ ናቸው ከሚባሉት አገሮች ተርታ የሌለችው ኢትዮጵያ በዓለም ውስጥ በዚህ ርእስ ጉዳይ ከተጠቀሱት 170 አገሮች መካከል ኢትዮጵያ እንዲያውም 111ኛው ሰልፍ ላይ ትገኛለች። ታዲያ የEthiopian Review ድረ ገጽ ባለቤትና አዘጋጅ ምን አደረገ ልትሉ እንደምትችሉ እገምታለሁ። እሱ ምኑ ሞኝ ነው በተገኘው ሁሉ ኢትዮጵያን ጭራ ማድረግ አይደል የሚፈልገው?

ታድያንላችሁ እንዲህ አለ "ኢትዮጵያ በንቅዘትና በሙስና ከተጨማለቁት 10 አገሮች ተርታ እንዳትገባ" Transparency International የተሰኘው ድርጅት ተወካዮቹን ወደ አዲስ አበባ ልኮ የመስክ ጥናት ሳያደርግ ባለበት ቦታ ላይ ሆኖ አንድ የወያኔ መንግሥት ተወካይ ቢሮ ቁጭ ብሎ የሚልክለትን መረጅ ተንተርሶ በመሥራቱ እንጂ ኢትዮጵያ እርግጠኛ ነኝ በሙስና ከተዘፈቁት 10 አገሮች አንዷ ትሆን ነበር ብሎ አረፈው።

ድንቄም ምሁራዊ ትንተና የምን ጉድ ነው ዘንድሮ የምንሰማው እዚሁ ቁጭ ብሎ ተጨፈኑና ላሞኛችሁ እኮ አንድ ነገር ነው ግን ጭልጥ ያለ ፀረ ኢትዮጵያዊነትና ፀረ ወገን አቋም ምን ይሉታል። እግዚአብሔር ያቺን አገር ክፉ ከሚመኙላት ዲያብሎሶች ይታደጋት ከማለት ውጪ ምን ይባላል?

ታዲያ ጽሁፌን ከመቋጨቴ በፊት ያቺ የcorruption index ጽሑፍ በአንዳች ምትሃታዊ ቅጽበት እብስ ብላ ከEthiopian Review ድረ-ገጽ ጠፍታለች አንዴ ሰይጣናዊ ምኞቱን አሳክቻለሁ ብሎ ይሁን ሰዎች አሁንስ ዓይን ያወጣ ምቀኝነት ይታይብሃል ብለውት አይታወቅም፤ጽሁፉ ግን ተነስቷል።